4

# <u>መንግስታዊ መሥሪያ ቤቶች፣ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ስለሚያስገቧቸው ዕቃዎች የወጣ መመሪያ ቁጥር 79/2005</u>

የኢትጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

መስከረም 2005 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# መንግስታዊ መሥሪያ ቤቶች፣ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ስለሚያስገቧቸው ዕቃዎች የወጣ መመሪያ ቁጥር 79/2005

መንግስታዊ መሥሪያ ቤቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወደአገር ውስጥ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ስለሚያስገቧቸው የልማት ዕቃዎችና መሣሪያዎች የወጣውን መመሪያ ቁጥር 17/1996ን ከኢንቨስመንት፣ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት እና ከሌሎች ህጎች ጋር ማጣጣምና የበለጠ ግልፅ ማድረግ በማስፈለጉ፣

ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ የሚገባው ዋናው ዕቃና መለዋወጫው በተለያየ ጊዜ ወይም ከተለያየ አገር የሚገባ በሚሆንበት ጊዜ መለዋወጫው ዘግይቶ እንዲገባ የሚፈቀድበትን ጊዜ መወሰን በማስፈለጉ፣

ባለሥልጣኑ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ደንብን ለማሻሻል ባወጣው ደንብ ቁጥር 89/1995 አንቀፅ 2 (1) (ሀ) እና 2 (2) (ሀ) እንዲሁም በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 112(2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "መንግስታዊ መሥሪያ ቤቶች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ስለሚያስገቧቸው ዕቃዎች የወጣ መመሪያ ቁጥር 79/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም፡-

1) "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፤
2) "ዕቃ" ማለት ተሽከርካሪ፣ የልማት ዕቃዎችና መሣሪያዎች ሲሆን መለዋወጫን ይጨምራል፡፡
3) "የልማት ዕቃዎችና መሣሪያዎች" ማለት አንድን የልማት ፕሮጀክት ለማስፈፀም ወይም ተግባራዊ ለማድረግ የሚያገለግሉ ቋሚ መሣሪያዎች፣ ዕቃዎችና

መለዋወጫዎች (Accessories) ሲሆኑ አላቂ ዕቃዎችን፣ የፍጆታ ዕቃዎችን፣ የቢሮ መገልገያዎችን፣ የቤት የግንባታ ዕቃዎችን፣ የኤሌክትሮኒክስ እና የኦዲዮቪዥዋል መሣሪያዎችን አይጨምርም፡፡ ሆኖም ለትምህርት መርጃነት የሚያገለግሉትን እንደ ኦቨር ሄድ ፕሮጀክተር (over head projecter)፣ ስላይድ ፕሮጀክተር (slide projecter)፣ ኮምፒዩተር፣ ፕሪንተር ሶፍትዌር (Printer software) እና የማባዣ መሣሪያዎችን ያካትታል፡፡

4) "የመንግስት መ/ቤት" ማለት ራሱን ችሎ በአዋጅ ወይም በደንብ የተቋቋመና ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ከመንግስት በሚመደብለት በጀት የሚተዳደር ሆኖ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ወይም የክልሉ አስፈፃሚ አካል በሚያወጡት የመንግስት መስሪያ ቤቶች ዝርዝር ውስጥ የተካተተ የፌደራል ወይም የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር መስሪያ ቤት ነው፡፡

5) "የበጎ አድራጎት ድርጅት" ማለት ለበጎ አድራጎት አላማ ብቻ የተቋቋመና ለህዝብ ጥቅም የሚሰጥ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ የተመዘገበ ድርጅት ነው፡፡

6) "ማህበር" ማለት በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ የተመዘገበ ሆኖ ዓላማው ትርፍ ለማግኘት ያልሆነ የአባላቱን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ እና ተመሳሳይ ሕጋዊ ዓላማዎችን ለማከናወን እንዲሁም ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ተቋማት ጋር ለመተባበር በአባላቱ ስምምነት የተመሠረተ የሰዎች ስብስብ ነው፡፡

7) "ከፍተኛ ትምህርት ተቋም" ማለት በስነጥበብ፣ ማሕበራዊ ሳይንስ፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ መስኮች በቅድመ ምረቃና ድህረ ምረቃ የዲግሪ ፕሮግራሞች ትምህርትና ስልጠና የሚሰጥ፣ ምርምር የሚያካሂድ እና ለማህረሰብ አገልግሎት የሚሰጥ የመንግስት ወይም የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ማለት ነው፡፡

8) "የኤክስቴንሽን ፕሮግራም" ማለት የሰብል ምርት ልማትን ወይም /እና የእንስሳት ልማትን ለማሻሻል የሚያስችሉ ዘዴዎችን ወይም/እና የድህረ ምርት ቴክኖሎጂን ማስተዋወቅን እንዲሁም የጤና እና የትምህርት አገልግሎት ፕሮግራም ነው፡፡

9) "ተሽከርካሪ" ማለት የደረቅ ወይም የፍሳሽ ወይም ዝቃጭ ማስወገጃ ወይም ፍሪጅ የተገጠመለት የጭነት መኪናን፣ ሞተር ብስክሌትን፣ ፒክ አፕን፣ ስቴሽን ዋገንን፣ ቶም ካርን፣ የሠራተኛ ማጓጓዣ አውቶብስን፣ ሚኒባስን፣ ጀልባን እና ዴሊቨሪ ቫንን ብቻ የሚያካትት ሲሆን ሀመርን፣ ካዲላክን እና ሌሎች ባለስልጣን

መስሪያ ቤቱ ወደፊት የሚወስናቸውን ተመሳሳይ ተሽከርካሪዎችን አይጨምርም፡፡

10)"አውቶብስ" ማለት ታጣፊ ወንበሮችን ሳይጨምር ቢያንስ 45 (አርባ አምስት) መቀመጫ ያለው የሰው ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ነው፡፡

11)"ሚኒባስ" ማለት ታጣፊ ወንበሮችን ሳይጨምረ ከ10 (አስር) ያላነሰ እና ከ12 (አስራ ሁለት) ያልበለጠ መቀመጫ ያለው የሰው ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ነው፡፡

12)"ሞተር ብስክሌት" ማለት ክብደቱ ከ400 ኪሎ ግራም የማይበልጥ ከሦስት መንኮራኩር /wheels/ በታች ያለው ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

1) ይህ መመሪያ መንግስታዊ መሥሪያ ቤቶች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ወደሀገር ውስጥ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ በሚያስገቧቸው የልማት ዕቃዎችና መሣሪያዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር 1 ድንጋጌ ቢኖርም መንግስት በዓለም አቀፍ የሁለትዮሽ እና የብዙሃን መንግስታት ስምምነት (Bilateral and Multilateral Agreement) መሰረት ለሚያቋቁሚቸው የመንግስት ፕሮግራሞች ወይም ፕሮጀክቶች እንዲሁም ከፌደራል ግብርና እና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ወይም በህግ ሥልጣን ከተሰጠው የመንግስት አካል ጋር የአጠቃላይ አተገባበር ስምምነት ሠነድ (General Operational Agreement) የሌላቸው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በሚያስገቧቸው ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ለመፍቀድ ስለሚቀርቡ ሠነዶች</u>

4. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው ሰነዶች

1) የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የቀረጥ ነፃ መብት ለማግኘት፡-

ሀ. ፕሮጀክቱ በፌደራል መንግስት ወይም በክልል መስተዳደር መ/ቤት የፀደቀ ስለመሆኑ ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ጋር የተፈረመ የስምምነት ሰነድ፣

ለ. ስምምነት የተደረሰበት ፕሮጀክት ፕሮፖዛል፣

ሐ. ድርጅቱ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ የተመዘገበ መሆኑን የሚያረጋግጥ የታደሰ የማህበራት ምዝገባ ሠርተፊኬት፣

መ. የዕቃው ማስጫኛ (Bill of Lading) ሰነድ በእንግሊዘኛ ወይም በአማርኛ የተዘጋጀ፡ ፡

ሠ. ዕቃው የተገዛበት ደረሰኝ (Invoice) በእንግሊዘኛ ወይም በአማርኛ የተዘጋጀ

ረ. የዕቃው ማሸጊያ ዝርዝር (Packing List) በእንግሊዘኛ ወይም በአማርኛ የተዘጋጀ፣

ሰ. የልማት ዕቃው በዕርዳታ የተገኘ ከሆነ የስጦታ ምስክር ወረቀት (Donation Certficate) በእንግሊዘኛ ወይም በአማርኛ የተዘጋጀ፣

ሸ. የሚመለከተው የመንግስት አካል የፃፈው የትብብር ደብዳቤ እና

ቀ. ድርጅቱ ከፌደራል ግብርና ሚኒስትር ወይም ከሚመለከተው አካል ጋር የተፈራረመው የአጠቃላይ የአተገባበር ስምምነት ሠነድ (General Operational Agreement) (ለመጀመሪያ የቀረጥና ታክስ ነፃ ጥያቄ ብቻ) ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1)/ሀ/ ድንጋጌ ቢኖርም የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ፕሮጀክቱ በፌዴራል መንግሥት ወይም ክልል መስተዳደር መ/ቤት የፀደቀ ስለመሆኑ ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ጋር የተደረሰ ስምምነት ሳይኖራቸው በተደረገ ጉብኝት ወይም ውጭ አገር ባሉ ለጋሾች በግል ተነሳሽነት የሚደረጉ እርዳታዎች ሲያጋጥሙ ዕቃውን በዋስትና በማውጣት ሰነዶቹን ሊያሟሉ ይችላሉ፡፡

5. ማህበራት የቀረጥ ነፃ መብት ለማግኘት:-

ሀ. ፕሮጀክቱ በፌደራል መንግስት ወይም በክልል መስተዳደር ወይም በከተማ አስተዳደር መ/ቤት የፀደቀ ስለመሆኑ ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ጋር የተደረሰ የስምምነት ሰነድ፣

ለ. ማህበሩ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ የተመዘገበ መሆኑን የሚያረጋግጥ የታደሰ የማህበራት ምዝገባ ሠርተፊኬት፣

ሐ. ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚገባው ዕቃ ለበጎ አድራጎት ዓላማ ብቻ የሚውል መሆኑን የሚያረጋግጥ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ ሰነድ፤

መ. የዕቃው ማስጫኛ (Bill of Lading) ሰነድ በእንግሊዘኛ ወይም በአማርኛ የተዘጋጀ፡ ፡

ሠ. ዕቃው የተገዛበት ደረሰኝ (Invoice) በእንግሊዘኛ ወይም በአማርኛ የተዘጋጀ

ረ. የዕቃው ማሸጊያ ዝርዝር (Packing List) በእንግሊዘኛ ወይም በአማርኛ የተዘጋጀ፣

ሰ. የልማት ዕቃው በዕርዳታ የተገኘ ከሆነ የስጦታ ምስክር ወረቀት (Donation Certficate) በእንግሊዘኛ ወይም በአማርኛ የተዘጋጀ፣

ሸ. የሚመለከተው የመንግስት አካል የፃፈው የትብብር ደብዳቤ እና

ቀ. ማህበሩ ከፌደራል ግብርና ሚኒስትር ወይም ከሚመለከተው አካል ጋር የተፈራረመው የአጠቃላይ የአተገባበር ስምምነት ሠነድ (General Operational Agreement) (ለመጀመሪያ የቀረጥና ታክስ ነፃ ጥያቄ ብቻ) ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፤

6. መንግስታዊ መ/ቤቶች የቀረጥ ነፃ መብት ለማግኘት፡-

   ሀ. መሥሪያ ቤቱ (ድርጅቱ) የፃፈው ማመልከቻ፤

   ለ. ለልማት ዕቃው ወይም መሳሪያው መግዣ በጀት የተፈቀደበት፤

   ሐ. የማስጫኛ ሰነድ (Bill of Lading) በእንግሊዘኛ ወይም በአማርኛ የተዘጋጀ፤

   መ. ዕቃው የተገዛበት ደረሰኝ (Invoice) በእንግሊዘኛ ወይም በአማርኛ የተዘጋጀ፤

   ሠ. የዕቃው ማሸጊያ ዝርዝር (Packing List) በእንግሊዘኛ ወይም በአማርኛ የተዘጋጀ እና

   ረ. ከለጋሽ ድርጅቶች /ግለሰቦች በተደረገ ስምምነት መሠረት ለሚካሄዱ ፕሮጀክቶች ለለጋሾች የቀረበ የፕሮጀክት ዕቅድ ፕሮፖዛል የስምምነት ሰነድ እና የስጦታ ምስክር ወረቀት (Donation Certficate) ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

7. የከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት የቀረጥ ነፃ መብት ለማግኘት፡-

   ሀ. ተቋሙ የፃፈው ማመልከቻ፤

   ለ. የስምምነት ሰነድ እና የፕሮጀክት ጥናት፤

   ሐ. የማስጫኛ ሰነድ (Bill of Lading) በእንግሊዘኛ ወይም በአማርኛ የተዘጋጀ፤

   መ. ዕቃው የተገዛበት ደረሰኝ (Invoice) በእንግሊዘኛ ወይም በአማርኛ የተዘጋጀ፤

   ሠ. የዕቃው ማሸጊያ ዝርዝር (Packing List) በእንግሊዘኛ ወይም በአማርኛ የተዘጋጀ፤

   ረ. የልማት ዕቃው በዕርዳታ የተገኘ ከሆነ የስጦታ ምስክር ወረቀት (Donation Certficate) እና

   ሰ. ከትምህርት ሚኒስቴር የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ከቀረጥና ታክስ ነፃ ስለሚገቡ ዕቃዎች አወሳሰን

8. ስለጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ መብት አወሳሰን

1) ባለሥልጣኑ ለመንግስታዊ መስሪያ ቤቶች፣ የከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት የልማት ዕቃዎችና መሣሪያዎች ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲያስገቡ ከመፍቀዱ አስቀድሞ የሚቀርቡለት ጥያቄዎች ለፕሮጀክቱ ያላቸውን አግባብነት ይገመግማል፡፡

2) ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና በክፍል ሁለት መሰረት የተጠቀሱትን ሰነዶች አጣርቶ አግባብ ያላቸውን የልማት ዕቃዎችና መሣሪያዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ይፈቅዳል፡፡

3) ባለሥልጣኑ ኦቨር ሄድ ፕሮጀክተር (over head projector)፣ ስላይድ ፕሮጀክተር (slide projecter)፣ ፕሮጀክት ሶፍትዌር (project software) እና የማባዣ መሣሪያዎች በፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ ላይ በተገለፀው መሠረት በቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ይፈቅዳል፡፡

9. በቀረጥና ታክስ ስለሚገቡ ተጨማሪ ዕቃዎች

በአንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ (3) የተገለፁት ዕቃዎች በፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ ላይ ያልተገለፁና ከለጋሾች በበጎ አድራጎት መልክ በተጨማሪ የተገኙ ከሆነ ተገቢው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ተከፍሎባቸው እንዲገቡ ይፈቀዳል፡፡

10. አውቶብሶች፣ ሚኒ ባሶች እና ሞተር ብስክሌቶችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ስለማገባት

1) ባለሥልጣኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ለአረጋውያን፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለሕፃናት ማሳደጊያ፣ ኤች አይ ቪ ኤድስ በደማቸው ያለ ግለሰቦችን ለመንከባከብ ሥራ፣ የጎዳና ተዳዳሪዎችን ለመንከባከብና ለመርዳት ተግባር፣ ለቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል (Vocational Training Center) ለሚያካሂዱት የዕርዳታ ተግባር አግባብ ካለው የፌደራል ወይም የክልል መንግስት መስሪያ ቤት ድጋፍ እስካገኙ ድረስ ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው ሠንጠረዥ መሰረት ሚኒ ባሶችንና/ወይም አውቶብሶችን ከውጪ ሀገር ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲያስገቡ ይፈቅዳል፡፡

| ተራ ቁ. | በአንድ ማዕከል የታቀፉ ተረጂዎች ብዛት | የሚፈቀደው የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት |
|---|---|---|
| 1. | ከ15–30 | 1 (አንድ) ሚኒ ባስ |
| 2. | ከ31–60 | 2 (ሁለት) ሚኒ ባስ |
| 3. | ከ61-90 | 1 (አንድ) አውቶብስ |
| 4. | ከ91 በላይ | 2 (ሁለት) አውቶብስ |

2) የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት ለሚያካሂዷቸው ፕሮጀክቶች አግባብ ካለው የፌዴራል ወይም የክልል መንግስት መስሪያ ቤት ወይም የከተማ አስተዳደር ድጋፍ እስካገኙ ድረስ የሞተር ብስክሌቶችን ከውጪ አገር ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲያስገቡ ይፈቅዳል፡፡

11.<u>የተለያዩ ተሽከርካሪዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ስለሚገቡበት ሁኔታ</u>

1) መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ለሚካሄድ ለማንኛውም ፕሮጀክት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ እንዲገባ የሚፈቀደው ተሽከርካሪ ዓይነት ፎር ዌል ድራይቭ፣ ፒክ አፕ ወይም እስቴሽን ዋገን ሆኖ የሚፈቀደው የተሽከርካሪ ብዛት በዋጋ ከፕሮጀክቱ ካፒታል 10% (አስር በመቶ) ሳይበልጥ <u>ሁለት</u> ብቻ ይሆናል፡፡

2) ለመንግስታዊ መ/ቤቶች የሚፈቀደው የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት በወቅቱ በስራ ላይ ያለውን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብን መሰረት በማድረግ የኢንቨስትመንት ቦርድ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

12.<u>መለዋወጫዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ስለማስገባት</u>

1) ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ለገቡ ዕቃዎች የመለዋወጫ አገልግሎት የሚውሉ ዋጋቸው ከዕቃዎቹ ዋጋ ከ15% (አስራ አምስት በመቶ) የማይበልጡ የመለዋወጫ ዕቃዎች ዋናው ዕቃ ከገባበት ቀን ጀምሮ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ከገቡ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲገቡ እንደ አግባብነቱ ባለሥልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ ቢኖርም በአንቀፅ (10) እና (11) ለተገለፁት ተሽከርካሪዎች እና የሞተር ብስክሌቶች መለዋወጫዎች ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ አይፈቀድም፡፡

13. <u>ሌሎች ዕቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ስለማገባት</u>

መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚያካሂዱቸውን የልማት ፕሮጀክቶች ዓላማ ለማሳካት የሚያገለግሉና ለፕሮጀክቱ ቀጥተኛ አግባብነት ያላቸውን እንደ ኩርየር ትራክ፣ አምቡላንስ፣ ክሬን፣ ማውንትድ ትራክ በፕሮጀክቱ ጥናትና ስምምነት በተመለከተው መጠን ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ማስገባት ይችላሉ፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

14. <u>የተከለከለ ተግባር</u>

በበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወይም የትምህርት ተቋም ስም ለንግድ ስራ ለተሰማሩ መሰል ተቋማት አገልግሎት በዚህ መመሪያ ሽፋን ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ አስገብቶ መጠቀም ክልክል ነው፡፡

15. <u>ቅጣት</u>

ይህን መመሪያ በመተላለፍ የቀረጥ ነፃ መብቱን አላግባብ የተገለገለ መንግስታዊ መሥሪያ ቤት፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም፣ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይንም ማህበር አግባብ ባለው ህግ መሠረት በወንጀል ይጠየቃል፡፡

16. <u>የተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች</u>

መንግስታዊ መስሪያ ቤቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወደ አገር ውስጥ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ስለሚያስገቧቸው የልማት ዕቃዎችና መሣሪያዎች ወጥቶ የነበረው መመሪያ ቁጥር 17/1996 ተሽሯል፡፡

17. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ መመሪያ ከመፅናቱ በፊት ተጀምረው ውሳኔ ያላገኙ ጉዳዮች በዚህ መመሪያ ውሳኔ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

18. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በዋና ዳይሬክተሩ ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ-------------------2005 ዓ.ም

መላኩ ፈንታ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር